# የመላው ዐማራ ሕዝብ ፓርቲ
# All Amhara People's Party



Telephone፡ +251920126061 Email፡ aapoallamhara@gmail.com Website፡ www.aapo-mahd.org

**ሰኔ 18 / 2011 ዓ.ም**

## ከመላው ዐማራ ሕዝብ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ !

ሰፊው የዐማራ ሕዝብ ሆይ !

ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በከፋ መንገድ በሕልውናህ ላይ ከፍተኛ አደጋ ተጋርጧል።

ሰኔ 15/2011 ውቢቷ ባህር ዳርን በደም ጎርፍ በማጥለቅለቅ በዐማራ ታሪክ ውስጥ መጥፎ ጠባሳ ጥሎ ያለፈው ጨለማው ቅዳሜ የዐማራን የማንነትና የሕልውና ትግል ፈተና ውስጥ ጥሎ አልፏል ። በዚህ ዕለት የተፈጸመው አሰቃቂ የግፍ ተግባር ውድ የዐማራ ልጆችን እና የወገኖቻችን ኢትዮጵያዊያንን ሕይወት ቀጭቷል። ከዐማራ ክልል ዶ/አምባቸው መኮንን (የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር)፤ አቶ እዘዝ ዋሴ (የድርጅት ጉዳይ አማካሪ)፤ አቶ ምግባሩ ከበደ (የክልሉ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ)፤ ብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ (የክልሉ የጸጥታና ደህንነት ጉዳይ ሃላፊ) እንዲሁም በአዲስአበባ ጀነራል ሰዓረ መኮንን (የኢትዮጵያ መከላከያ ስራዊት ኤታማጆር ሹም) እና ሜ/ጀነራል ገዛኢ አበራ ባልጠበቁት ግድያ ሕይወታቸው አልፏል።

በዚህ ወሳኝና መራራ ቀን ለሕልውናህ በምታደርገው ተጋድሎ መዐሕፓ ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ከጎንህ ነው። የተፈጸመውን ግድያ በጥብቅ እያወገዝን ልባዊ ሃዘናችንን በመግለጽ ለቤተሰቦች መጽናናትን እንመኛለን።

የመላው ዐማራ ሕዝብ ፓርቲ ፣ 1 . ይህን ያልተጠበቀ ግድያ ለመመርመር ነጻና ገለልተኛ የሆነ ቡድን በአስቸኳይ እንዲቋቋም ፣ ሕዝብ መረጃ የማግኘት መብቱ ይጠበቅ ዘንድ ነጻ ጋዜጠኞችን በማዋከብ የማህበራዊ የመገኛኛ አውታሮችን በመዝጋት የአንድ ወገን የተዛባ መረጃ ማስተላለፍ ለባሳ አደጋ የሚጋብዝ መሆኑን መንግስት በጽኑ ሊረዳና የኢንተርኔት ግልጋሎትን ክፍት እንዲያደርግ ይጠይቃል ። በማያያዝም ይህን አደጋ እንደ አጋጣሚ ተጠቅመው በዐማራ ሕዝብ ላይ የስነልቦና ተጽእኖ ለማሳደር የሚሯሯጡ ኃይሎች ከዚህ እኩይ ተግባር እንዲታቀቡ እንመክራለን ።

በዐማራው ሕዝብ ላይ የሚፈጸመው ሴራ በአስቸኳይ ይቁም !

በተባበረ የዐማራ ሕዝብ አንድነት ዐማራው ሕልውናውን ያስከብራል !

/